# ለኦሮሞው ቆሞ አማራውን የሚቃወም ሌላውን አይዞህ አማራን ይውጋህ የሚል ከአንበሳው ጋይንት የተገኘ አማራ ነው ብየ አላምንም

October 13, 2016

ልጅ እያለን ትምህርት ቤት “ስታድጉ ምን መሆን ነው የምትፈልጉት? ተብለን ስንጠየቅ እኔን ጨምሮ የክፍሉ አብዛኛው ተማሪ “ልክ እንደ ታማኝ በየነ” እያልን እንመልስ ነበር፡፡በተለይ አስቻ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ስንማር እዚያው ት/ቤት የምታስተምረው የታማኝ በየነ እህት ኤልሳ በየነ ምን መሆን እንደምንፈልግ ስትጠይቀንማ እትየ ኤልሳን ለማስደሰትም ጭምር ሲል ሁሉም ተማሪ “ልክ እንደ ታማኝ” እያለ ይመልስ ነበር፡፡እትየ ኤልሳ ታድያ ክፉም በጎም ሳትናገር ፈገግ ብላ ማስተማሯን ትቀጥላለች፡፡ የጋይንቷ ርዕሰ ከተማ ነፋስ መውጫ የታማኝ በየነ የትውልድ ከተማ በመሆኗ ታማኝ በየነን የማያውቅ የማያደንቅ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ ስማርት ሀብታሙ ዘውዴ አድና ሀይሌ ጌትነት…. ቪድዮ ቤቶች ረዘም ላሉ አመታት የታማኝ ስራዎች ፊልሙ ከመጀመሩ በፊት መቅረባቸው የግድ እስኪመስል ድረስ አይቀሩም ነበር፡፡ ወያኔ እገዳ እስከጣለበት ጊዜ ድረስም የታማኝ ፎቶ በነፋስ መውጫ ፎቶ ቤቶች ግድግዳ ላይ አይጠፋም ነበር፡፡በየቤቱ ግን እንደ ወትሮው ባይሆንም ዛሬም አለ፡፡ በወቅቱ ስለ ፖለቲካ ያለን ግንዛቤ እጅግ አናሳ የነበረ ቢሆንም ታማኝ የጋይንት ልጅ በመሆኑና ጋይንትን በማስጠራቱ እጅግ እንኮራ ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ ግን በሙብራት እጦት በምትጠራሞሰው በነፋስ መውጫ አናት ላይ የተዘረጋው የሙብራት ገመድ ነፋስ መውጫን ብቻም ሳይሆን አያሌ የአማራ ከተሞችን ቁልቁል እየተመለከተ አልፏቸው ወደ ትግራይ በመጓዙ ህዝብ በጆሮው የሚሰማውን የወያኔን የለየለት አድሏዊ አሰራር በአይኑ የተመለከተበት ጊዜ በመሆኑ አንቀሳቃሽ ይሻ ነበር፡፡ ታማኝንም እንደ ታዳጊ ይቆጥረው ነበር፡፡

ታማኝ በየነ የቅርብ እንኳ ባይሆን ዘመዴ ነው፡፡ ከዝምድና በላይ ግን የእርሱና የኔ ቤተሰቦች የጠበቀ ወዳጅነት ስላላቸው ከቤታቸውም ሆነ ከሆቴላቸው(የቀድሞው ጎንደር በር ሆቴል) አልጠፋም ነበር፡፡የታማኝ በየነ የእህቱ ልጅ ቴዎድሮስ(እያያለም) ጌታቸውም የልብ ጓደኛየ ነው፡፡ ከታማኝ ቤተሰቦች ጋር መቀራረቤም ስለማደንቀው ስለምወደው ታማኝ በየጊዜው መረጃ የማግኘት እድልን ፈጥሮልኛል፡፡ምንም እንኳን በወቅቱ ታማኝን በስልክ ለማግኘት አደርገው የነበረው ጥረት ባይሳካም፡፡

ሰሞኑን ትዝ ብሎኝ ታማኝን መሆን ሲመኝ የነበረውንም ታማኝን ሲያደንቅ የነበረውንም ስጠይቅ ግን ውጤቱ ከወትሮው ተቃራኒ ሆኖ አገኘሁት፡፡ አዲሱ ትውልድማ ታማኝ በፖለቲካው አለም ይህን ያህል ተሳትፎ እያለው ለውጥ በማያመጣ መነሻ እንጂ መድረሻ በሌለው ጎዳና ገብቶ ሲዳክር በመኖሩ አማራ በአማራነቱ ሲጠቃ እየተመለከተ አማራ እንዳይደራጅ ሲከላከል በመኖሩ አሁንም አማራ መደራጀት ጀመረ ሲባል የተለመደ የጎጥ መቀሱን ይዞ መሰለፉ አሳዝኖታል፡፡ በታማኝ ያሳደገው የጋይንት ህዝብ ብቻም ሳይሆን መላው አማራነት የገባው አማራ ጥርሱን ነክሷል፡፡

ታማኝ በየነ ጉም ሊዘግን በከንቱ አንድነት አንድነት እያለ አማራውን ሲያዘናጋ ኖሯል፡፡ የኦሮሞውን የትግሬውን የጋምቤላውን…. መደራጀት ሲደግፍና በጉባኤያቸው እየተገኘ አይዟችሁ ከጎናችሁ ነን ሲል በአንፃሩ አማራ በአማራነቱ እንዳይደራጅ በስውርም በግልፅም ሲሰራ ኖሯል እየሰራም ነው፡፡ አዎ ታማኝ ዘመዴ ነው ቤተሰቦቹም ቤተሰቤ ናቸው አማራ እንዳይደራጅና አማራ ራሱን ከጥቃት እንዲከላከል የማትሻ ከሆነ ግን ታማኝ አይደለም እናቴም ትቅርብኝ!

ለኦሮሞው ቆሞ አማራውን የሚቃወም ሌላውን አዞህ አማራን ይውጋህ የሚል ከአንበሳው ጋይንት የተገኘ አማራ ነው ብየ አላምንም፡፡ ታማኝ ብዙ መድከሙ ባይካድም የደከመው ግን የማይለወጥን ለመለወጥ በመሆኑ ድካሙ የሚያስመሰግነው ሳይሆን የሚያስወቅሰው ሆኗል፡፡ አማራ ላይ ብቻ ኢትዮጵያዊነትን ለመጫን ሲጣጣር አማራን አስጨርሷል፡፡ የመከራ ዘመኑን አራዝሟል፡፡ ያገኘውን እውቅና ተጠቅሞ አማራ በአማራነቱ እንዳይቆም ደፍሮ አማራ ነኝ እንዳይል ብዙ ሰርቷል።

አሁን ደግሞ ያ ሁሉ በደሉ አንሶት አማራ አንድ መሆን ሲጀምር የጥፋት እጁን መስደድ ጀምሯል፡፡ከኢትዮጵያዊነቴ ንቅንቅ አልልም ሲል የነበረው ሰው ዛሬ ጎንደሬ ሆኖ መጥቷል፡፡ በአማራነት መደራጀትን ማነስ ያለ ሰውየ ዛሬ በጎንደሬነት መደራጀትን ሊደግፍ እግረ መንገዱን ገንዘብ ሊቃርም ከረጢቱንም መርዙንም ይዞ መጥቷል፡፡ ሁለሉም ተደራጅቶ አማራ ብቻውን ቆሞ የማንም ኢላማ መለማመጃ ሲሆን ያልቆጨው የጥፋት ልጅ ዛሬ አማራን ሊበትን የእድር ካባ ለብሶ መጥቷል፡፡ አማራ ድምፁ እንዳይሰማ አማራ በአማራነት ይደራጅ የሚል ሰው የኢሳትን ስቱዲዮ እንዳይረግጥ ስውር ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ የነበረው ዳግማዊ መለስ ዛሬ አማራ አንድ እንዳይሆን አሸከላውን ዘርግቷል፡፡ አማራነትን ንቆ ከአማራ ማዕድ ሊቋደስ እጁን ሰዷል፡፡

## የዐማራ ተጋድሎ ይቀጥላል !!!